DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

ስልታዊ እቅድ

# ሃሳብ መግለጽ እና ማሻሻል
# የ2022 ተሳትፎ ማጠቃለያ







DCPSstrong.com

GOVERNMENT OF THE
DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR









DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# ደብዳቤ ከ ዩንቨርሲቲ ሃላፊው

ጃንዋሪ 2023

## ሰላም የ DC የህዝብ ትምህርት ቤቶች ማህበረሰብ፣

እያንዳንዱ የትምህርት ዘመን በአንድ ልጅ የትምህርት ጉዞ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ ያመለክታል— አዲስ ጓደኝነት ለመመስረት፣ የግል ፍላጎቶችን ማጠናከሪያ፣ እና ወደ ምርቃት እና ሌላ እርምጃ ለመውሰድ ጊዜ። ህዝባችን ወረርሽኙ፣ የዘር ኢፍትሃዊነት፣ የጦር መሳሪያ ጥቃት፣ እና ከሌሎችም ተጽዕኖዎች ጋር መታገሉን በቀጠለበት ወቅት ተማሪዎች ይህን እያደረጉ ነው።

ከእነዚህ ትውልድን የሚወስኑ ጊዜዎች ከበፊቱ የበለጠ ጠንክረን መውጣት የእኛ ቁርጠኝነት ነው። ከሚደግፉን ቤተሰቦቻችን፣ ከተሳታፊ ማህበረሰብ፣ እና ችሎታ ካለው የDC የህዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) ቡድን ጋር በመሆን፣ እያደግን ነው። እድገትን ለማፋጠን ያለን ቁርጠኝነት የተመሰረተው እንደ አንድ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ራዕያችንን ለመምራት እንዲያግዝ የማህበረሰቡን ድምጾች ማዕከል ባደረገው የአምስት አመት ስልታዊ እቅዶቻችን ላይ ነው።

የአብይ ቁርጠኝነት ስልታዊ እቅድ፣ በ2012 ለመጀመሪያ ጊዜ የተጀመረው እና በ2017 የተሻሻለው፣ በትምህርት ፍትሃዊነት እና በተማሪ ስኬት ማዕከል ያደረገ የትምህርት ስርዐት እንዲሆን የDCPSን እውነተኛ ጥረት አስታውቋል።

በኦገስት 2022፣ DCPS ቀጣዩን የስልታዊ እቅዳችንን ድግግሞሽ ለመስራት የአንድ አመት የመመልከት እና የማሻሻል ጉዞ ጀምሯል። በበልግ ወቅት፣ በጠንካራ ጎኖቻችን ላይ እና የቱ ጋር ማደግ እንዳለብን ሃሳባቸውን እንዲገልጹ ለሰራተኞች፣ ለተማሪዎች፣ ለቤተሰቦች፣ እና የማህበረሰብ አባላት እድሎችን ጨምሮ፣ DCPS ተሳትፎ የመስማት ፕሮግራም አስተናግዷል።

በተለይም፣ በአራት ዋና ዋና ጥያቄዎች ዙሪያ አስተያየት ጠይቀናል፦

1። ለሁሉም ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ እና ሰራተኞች እንግዳ ተቀባይ እና ደጋፊ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ምን ይመስላል?

2። በሁሉም DCPS ፍትሃዊ ፕሮግራምን እና ፖሊሲዎችን ለማረጋገጥ ምን ማድረግ እንችላለን?

3። ተማሪዎቻችን ሙሉ አቅማቸው ላይ ለመድረስ በትምህርት፣ በማህበራዊ፣ እና በስሜት ምን ይፈልጋሉ?

4። ሁሉም ተማሪዎች እንዲያድጉ ሰራተኞቻችን፣ ቤተሰቦቻችን፣ እና ተማሪዎቻችን ምን አይነት መርጃዎች ያስፈልጋቸዋል?

ከማዳመጥ ክፍለ ጊዜዎች የወጡ ቁልፍ ንግግሮችን እና ጭብጥ መልዕክቶችን ለማጋራት ጓጉቻለሁ።

በዚህ አዲስ ስልታዊ እቅድ አማካኝነት፣ DCPS ወደ ትምህርት ፍትሃዊነት እና የተማሪ ስኬት ግቦቻችን ያለማቋረጥ ወደ ፊት መሄዱን ይቀጥላል። በዚህ የጸደይ ወቅት፣ የእኛን ረቂቅ የስልታዊ እቅድ ሃሳቦችን ለህዝብ እናጋራለን እና አዲሱን ስልታዊ እቅድ በበጋ 2023 እናጠናቅቃለን።

በአጋርነት፣

**ሌዊስ ዲ. ፌሬቤ፣ Ed.D.**
የዩንቨርሲቲ ሃላፊ



# ስልታዊ እቅዳችንን ማሻሻል

የተሳትፎ ግባችን ሁሉም የDCPS ባለ ድርሻ አካላት በወቅታዊ ስኬቶች ላይ የሚገነባውን እና በእያንዳንዱ ዙር ፍትሃዊነትን የሚገነባውን የቀጣዩን የአምስት አመት የDCPS ስልታዊ እቅድ በመቅረጽ መረጃ ያላቸው እና ተሳታፊ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው። ስልታዊ የእቅድ ሂደቱ በሚከተሉት አራት ምዕራፎች የተደራጀ ነው፦

---

| በጋ 2022 | በልግ 2022 | ክረምት እና ጸደይ 2023 | በጋ 2023 |
|---|---|---|---|
| ምዕራፍ 1 | ምዕራፍ 2 | ምዕራፍ 3 | ምዕራፍ 4 |
| ሃሳብ መግለጽ | መሳተፍ | መቅረጽ እና ማርቀቅ | ማጠናነቀቅ እና ማክበር |
| በ2017-2022 አብይ ቁርጠኝነት እና ጠቅላላ ውጤታችን ላይ ሃሳብ መግለጽ | በእድገታችን እና እድሎቻችን ዙሪያ አስተያየት እንዲሰጡ የማህበረሰቡን አባላት ማሳተፍ | ከያዝነው ግብዐት በመረጃ ላይ የተመሰረተ ቀጣይ ስልታዊ እቅዳችንን ረቂቅ መቅረጽ እና ለተጨማሪ ግብረ መልስ ማሰራጨት። | ከትምህርት ዘመን 2023-2024 የሚቀጥለውን ስልታዊ እቅድ ማጠናቀቅ |

> "ከምንም ቦታ ቢመጡ፣ ምንም አይነት መልክ ቢኖርዎት፣ እርስዎ ላይ የማይፈርድ ማህበረሰብ ያስፈልግዎታል።"
>
> – ተማሪ፣ Cardozo (ካርዶዞ) የትምህርት ካምፓስ ክፍለጊዜ

## ከማን ሰማን

በተሳትፎ ምዕራፍ ወቅት፣ DCPS ስድስት ቤተሰብን እና ማህበረሰብን የማዳመጥ ክፍለጊዜዎች፣ አራት ተማሪን የማዳመጥ ክፍለጊዜዎች፣ 21 ሰራተኞችን የማዳመጥ ክፍለጊዜዎች፣ አንድ የDCPS ርዕሰ መምህር ክፍለጊዜ እና ለተሳትፎ ሂደቱ ጥራት ያለው ግብአት ለመሰብሰብ አንድ የማህበረሰብ ጥምር ስብሰባ አስተናግዷል። የ DCPS ሰራተኞች የማዕከላዊ አገልግሎቶችን፣ የትምህርት ቤት ግቢ አመራርን፣ እና አስተማሪዎችን ያካትታሉ። ከቤተሰብ እና ከማህበረሰብ አባላት ጉልህ ተሳትፎ ያላቸው በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉትን የእያንዳንዱን ቀጠና የሚወክሉ ተሳታፊዎችን አሳትፈናል።

እንደ የማዳመጥ ክፍለ ጊዜ ተግባሮቻችን አካል፣ ታዳሚዎች በመተላለፊያ የእግር ጉዞ እና የአነስተኛ ቡድን ግብረ መልስ ላይ ተሳትፈዋል። በእነዚህ ልምምዶች ወቅት፣ ተሳታፊዎች በአራት ዋና ዋና ጥያቄዎች ዙሪያ አስተያየታቸውን እንዲያጋሩ ተጠይቀው ነበር። እነዚህ ጥያቄዎች የተሳትፎ ሂደታችን መጀመሪያ ላይ ተዘጋጅተው ነበር እናም በእያንዳንዱ የማዳመጥ ክፍለ ጊዜ ተጠይቀው ነበር። በማዳመጥ





ክፍለ ጊዜያችን የመተላለፊያ የእግር ጉዞ ክፍለጊዜዎች ከ400 በላይ ከሚሆኑ ቤተሰቦች፣ የማህበረሰብ አባላት፣ ተማሪዎች፣ እና የሰራተኞች ታዳሚዎች ወደ 600 የሚጠጉ በግብረመልስ የተደገፉ የ Post-It ማስታወሻዎችን ተቀብለናል።

### # Post-It አስተያየቶች ከመተላለፊያ የእግር ጉዞ



ቤተሰቦች/ የማህበረሰብ አባላት

ተማሪዎች

### የተሳታፊዎች ቁጥር በቡድን:-



ቤተሰቦች/ የማህበረሰብ አባላት

ተማሪዎች

ሰራተኞች

**ማስታወሻ:-** እያንዳንዱ ቁምፊ አስር (10) የpost-it አስተያየቶችን ወይም ተሳታፊዎችን ያመለክታል።

> “ብቃት ያላቸውን ሰራተኞቻችን ማቆየት ላይ ኢላማ ያደረጉ ሃብቶች... ለምን እና እንዴት ማቆየት እንደምንችል ለመወሰን ብዙ መሰራት አለበት።”
>
> \- DCPS የሰራተኛ ክፍለጊዜ

# የተሳትፎ ጭብጦች

ከዚህ በታች በተሳትፎ ምእራፍ ወቅት የተነሱ ዋና ዋና ጭብጦች ውህድ ሲሆን፣ በተለይም ሁሉም ባለድርሻ አካላት በተጠየቁት አራት ቁልፍ ጥያቄዎች ላይ ያተኮረ ነው። እያንዳንዱ ጭብጥ የተደራጀው ለእያንዳንዱ ጥያቄ ሃሳባቸውን እና አስተያየታቸውን ሲሰጡ ከዋና ዋና ባለድርሻ አካላት በተሰማው መሰረት ነው።

### ለሁሉም ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ እና ሰራተኞች እንግዳ ተቀባይ እና ደጋፊ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ምን ይመስላል?

ቤተሰብ/ ማህበረሰብ፦

- ከተማሪዎች ጋር እንግዳ ተቀባይ እና እምነት የሚጣልበት ግንኙነት ያለው የሰራተኛ ባህልን ማሳደግ።
- በቤተሰብ እና በትምህርት ቤት አመራር መካከል ያለውን ግንኙነት መጨመር እና ከትምህርት ቤት መሪዎች የበለጠ ግልጽነት።
- የተማሪዎችን ልዩነት የሚያቅፍ እና የበለጠ አካታች ለመሆን የሚሰራ የትምህርት ቤት ማህበረሰብን ማስፋፋት።
- ተጨማሪ ክበቦችን እና ከመደበኛ ትምህርት ውጪ ያሉ ተግባራትን ማሳደግ

ሰራተኞች/ መምህራን፦

- ሰራተኞች አድናቆት እንዳገኙ፣ አቀባበል እንደተደረገላቸው፣ እና ድጋፍ እንዳገኙ እንዲሰማቸው የሚያደርግ ማህበረሰብ ማስፋፋት
- የሚጠበቅባቸውን ለማሟላት የሚያስፈልጋቸውን መርጃዎች እና ስልጠናዎችን ለሰራተኞች ማቅረብ።
- ተግባራዊ የሆኑ ግምቶች መያዝ እና ሊደረስባቸው የሚችሉ ግቦችን ማስቀመጥ።
- በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ ሰራተኞችን ማካተት።

ተማሪዎች፦

- ለመማር ንጹህ እና በደንብ የተጠበቁ ቦታዎችን ማቅረብ።
- በሰራተኞች እና በተማሪዎች መካከል መከባበርን ማበረታታት።
- የተማሪዎችን ፍላጎት ማወቅ እና መፍትሄ መስጠት።
- በሰራተኞች እና በተማሪዎች መካከል የበለጠ መተማመንን መፍጠር።

ርዕሰ መምህራን፦

- አካላዊ ህንጻዎች ከDCPS መስፈርቶች ጋር እኩል ደረጃ እንዳላቸው ማረጋገጥ።
- ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤቱ ህንጻ እንደገቡ ሰራተኞች አዎንታዊ የሆነ ሰላምታ ማስቀደም።
- አካታችነትን ማሳዳግ እና የተለያዩ ባህሎችን፣ ብሄረሰቦችን፣ እና ኢኮኖሚያዊ ዳራዎችን ማወቅ።
- ሁሉንም የተማሪ ፍላጎቶች የሚያሟሉ መሆናቸውን በመጠየቅ፣ የትምህርት ቤት ፖሊሲዎችን እና ልምምዶችን በተከታታይ መገምገም።

### በ DCPS ፍትሃዊ ፕሮግራሞችን እና ፖሊሲዎችን ለማረጋገጥ ምን ማድረግ እንችላለን?

ቤተሰብ/ ማህበረሰብ፦

- በበጀቶች፣ በውሂብ፣ እና በትምህርት ቤቶች ውስጥ ምን እየተከሰተ እንዳለ በግልጽነት ማቅረብ።
- ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢን ማስፋፋት።
- አስተማሪ ማቆየትን ማሳደግ።

> "በብዝሃነት፣ በእኩልነት እና አካታችነት የባለሙያ እድገት መቀጠል እና ሃብቶች የሚገኙ ከሆነ የወላጅ ማህበረሰብን እንዲሳተፉ መጋበዝ።"
>
> \- ቤተሰብ/ማህበረሰብ አባል፣ ቨርቹዋል ክፍለጊዜ

ሰራተኞች/ መምህራን፦

- መምህራኖቻችን ፍትሃዊ ድጋፍ እና ማረጋገጫ ማግኘታቸውን ያረጋግጡ።
- ትምህርት ቤቶቻችንን እና ማህበረሰቡን ማዋሃድ።
- በክፍል ውስጥ የበለጠ የሚያሳስብ ትምህርትን ማሳደግ።

ተማሪዎች፦

- በስምንቱም ቀጠናዎች መካከል ፍትሃዊነትን ያረጋግጡ።
- ተጨማሪ ማስታወቂያዎችን በተለያዩ የመገናኛ መንገዶች ያሰራጩ።
- ሁሉም ተማሪዎች ተደማጭ እንደሆኑ እና የተወከሉ መሆናቸው ያረጋግጡ።
- ለኮሌጅ እና ለስራ እቅድ መርጃዎች የተመደቡ የተወሰኑ ሰራተኞች ማኖር።
- ለሁሉም ተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ የኮሌጅ እና የስራ እቅድ መርጃዎችን ማቅረብ።

ርዕሰ መምህራን፦

- ለተማሪዎች ከትምህርት ቤት በፊት እና በኋላ ፕሮግራምን ማዘጋጀት እና ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ መስጠት።
- ለ DCPS ፍትሃዊነት ምን ማለት እንደሆነ አውደ ጥናት ማዘጋጀት እና እሱን ለመተግበር ስርዐቶችን መፍጠር።
- በተማሪዎች ፍላጎቶች ላይ የተገደቡ የትምህርት ቤት በጀቶች ላይ ትኩረት ማድረግ።
- በዲስትሪክቱ ውስጥ ላሉ ትምህርት ቤቶች የሰራተኞች ፍላጎቶችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ማስተዳደር።

## ተማሪዎቻችን ሙሉ አቅማቸው ላይ ለመድረስ በትምህርት፣ በማህበራዊ፣ እና በስሜት ምን ይፈልጋሉ?

ቤተሰብ/ ማህበረሰብ፦

- ለተማሪዎች አስፈላጊ የህይወት ክህሎቶችን ለማስተማር ተጨማሪ የማበልጸጊያ እድሎችን መፍጠር።
- የተማሪዎችን ፍላጎት ለማሟላት የተለያዩ ፕሮግራሞችን ማቅረብ።
- ስኬታማ ተማሪዎችን እውቅና መስጠት እና ማክበር።
- ለተማሪዎች የአዕምሮ ጤና ድጋፍ መስጠት።

ሰራተኞች/ መምህራን፦

- መምህራን የተማሪዎቻቸውን ፍላጎት እንዲያሟሉ በመርጃዎች ማስታጠቅ።
- የተማሪዎችን ማህበረሰቦች ለመርዳት በማህበራዊ ስራ ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ።
- ለተሻለ የአዕምሮ ጤና ድጋፍ እድገት ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ማቅረብ።
- ተማሪዎችን ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ የሚያጎለብቱ ስርአተ ትምህርቶችን ማሳደግ።
- ተጨማሪ ከትምህርት ቤት ውጪ የሆኑ የማበልጸጊያ እድሎችን መፍጠር።

ተማሪዎች፦

- አጋዥ እና የሚያበረታቱ አስተማሪዎች ማቅረብ።
- ተማሪዎች በግልጽ የሚግባቡበት ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ማስፋፋት።



- ከትምህርት ቤት ውጭ የሆኑ ተጨማሪ የማበልጸጊያ ፕሮግራሞችን መፍቀድ።
- ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር የሚገናኝ አሳታፊ ፕሮግራም ማሳደግ።
- የተማሪ ድምጾችን ማግነን።

ርዕሰ መምህራን፦

- ቤተሰቦች ከDCPSን ለቀው የቻርተር ትምህርት ቤቶች የሚማሩበትን ዋና ዋና ምክንያቶችን መለየት።
- ለተማሪዎች ብዙ የቋንቋ መጃዎችን ማቅረብ።
- በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ ለሁለቱም ለተማሪዎች እና ለሰራተኞች የአዕምሮ ጤና ድጋፍ ስርዐቶችን መደገፍ።
- የትምህርት ቤት የገንዘብ ድጋፍ ከትምህርት ቤት እቅድ እና ግቦች ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማረጋገጥ።

## ሁሉም ተማሪዎች እንዲያድጉ ሰራተኞቻችን፣ ቤተሰቦቻችን፣ እና ተማሪዎቻችን ምን አይነት መርጃዎች ያስፈልጋቸዋል?

ቤተሰብ/ ማህበረሰብ፦

- ለማህበረሰብ እና ለቤተሰብ ተሳትፎ እድሎችን መፍጠር።
- ደህንነቱ የተጠበቀ የመጓጓዣ ተደራሽነት ማቅረብ።
- በማህበረሰቡ መካከል ግብረ መልስ እና ግልጽነትን ለማቅረብ ቀጣይነት ያለው ወቅታዊ የመስማት ክፍለጊዜዎችን ማዘጋጀት።
- የሁሉም ዳራ እና ችሎታዎች ብዝሃነት ማክበር።

ሰራተኞች/ መምህራን፦

- የሰራተኞች ምልመላ እና የማቆየት ጥረቶችን ማሻሻል።
- መምህራንን ለመደገፍ የገንዘብ ግብዐቶችን ማቅረብ።
- ለሰራተኞች እና ለአስተማሪዎች ድምጽ ቅድሚያ መስጠት።
- ለሰራተኞች፣ ተማሪዎች፣ እና ቤተሰቦች የአዕምሮ ጤና አቅራቢዎችን ተደራሽነትን የበለጠ ማቅረብ።

ተማሪዎች፦

- የትምህርት ቤት አቅርቦቶችን እና የቴክኖሎጂ ተደራሽነትን ማሳደግ።
- ለስፖርቶች እና ከመደበኛ ከትምህርት ውጪ የሚደረጉ ተግባራት ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ መመደብ።
- በትምህርት ቤቱ ውስጥ አንድ ማህበረሰብ መፍጠር።
- ተጨማሪ የተማሪ ተሳትፎን ያስፋፋት።
- ባህላዊውን የ5-ቀን የትምህርት ሳምንት እንደገና ማሰብ።
- ወቅታዊ የሃይማኖት ስነ ስርዐት የክፍል ቀናትን ፍትሃዊ ግምገማ ማካሄድ።

ርዕሰ መምህራን፦

- መምህራንን እና ሰራተኞችን ለማሰልጠን ተጨማሪ ግብዐቶችን ማቅረብ።
- የሰራተኞች ምልመላ እና የማቆየት ጥረቶችን መጨመር።
- የተማሪ ባህሎችን እና የጾታ መለያዎችን ማክበር።
- ለተማሪዎች ተጨማሪ የአዕምሮ ጤና መርጃዎችን እና የምክር አገልግሎት ማጎልበት።



# የማዳመጥ ክፍለ ጊዜ ማጠቃለያ

## ቤተሰብ እና ማህበረሰብ

DCPS ከአስተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ እና ሌሎች የማህበረሰብ አባላት ጋር በአካል እና በቨርቿል የተለያዩ ክፍለ ጊዜዎችን አስተናግዷል። **ከዚህ ውይይት የወጡ የተለመዱ ጭብጦች በትምህርት ቤት ደህንነት፣ በቤተሰብ ተሳትፎ፣ እና በፍትሃዊነት ላይ ያተኮሩ ናቸው።**

ደህንነቱ የተጠበቀ እና እንግዳ ተቀባይ የትምህርት ቤት አካባቢ መፍጠር የሚጀምረው በትምህርት ቤቱ ውስጥ እና በአካባቢው ያሉ ቦታዎች ንጹህ እና በጥሩ ሁኔታ የተያዙ መሆናቸውን በማረጋገጥ ነው። ከንጹህ ቦታዎች በተጨማሪ፣ ከተማሪዎች ጋር ጠንካራ ግንኙነት ያለው ቁርጠኛ ተቋም የደህንነት ስሜትን ይጨምራል። የሚኮሩበት ቦታ እና ከትምህርታቸው ባለፈ፣ በተለይም ስለ ተማሪዎች ደህንነት እና ደስተኛነት መሆን ዙሪያ ግድ የሚላቸው የሰዎች አውታረመረብ ማግኘት፣ የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ የሚያድግበት፣ የሚጎለብትበት፣ እና የሚቀጥልበት አካባቢ ለመፍጠር ያግዛል።

የቤተሰብ ተሳትፎን ለማበረታታት፣ ትምህርት ቤቶች ቤተሰቦች ከመምህራን እና ሰራተኞች ጋር እንዲገናኙ እና ጠንካራ የመተማመን አውታረ መረቦችን የመፍጠር እድሎችን ለመስጠት ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ ምሽቶች ወይም የበጋ ክፍት ቤቶች የመሳሰሉ ዝግጅቶችን ማዘጋጀት ይችላሉ። እንደ ስርዐተ ትምህርት ምሽቶች ያሉ እድሎች በወረርሽኝ ስጋቶች ምክንያት ተቋርጠው ነበር፣ እና ወላጆች እና ቤተሰቦች ተማሪዎችን በቤት ውስጥ እንዲያግዙ በተሻለ ሁኔታ ለማስታጠቅ እነዚህን ዝግጅቶች እንደገና ማደስ ይፈልጋሉ። እንዲሁም የማህበረሰቡ አባላት የትምህርት ቡድኖች እና ተጓዳኝ እንቅስቃሴዎች ወደ ቅድመ ወረርሽኝ ደረጃዎች እንደገና ሊጀምሩ እንደሚችሉ ተስፋ ያደርጋሉ።

በDCPS ስለ ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞች ፍትሃዊነት በመወያየት፣ የማህበረሰቡ አባላት ከአናኮስቲያ ወንዝ በስተምስራቅ ያሉ ትምህርት ቤቶችን እና ግብዐቶችን በማነጋገር ጥረቶች መጀመር እንዳለባቸው ተሰምቷቸዋል። ከወንዙ በስተምስራቅ ነዋሪ ያልሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን የግብዐት ስርጭት ፍትሃዊነት ጉዳዮችን ገልጸዋል። ኢፍትሃዊነትን ለመቅረፍ የቀረቡት ሃሳቦች የገንዘብ ድጋፎች እንዴት እንደሚመደቡ የበጀት ግልጽነትን መጨመርን እና በDCPS ፍትሃዊነትን ለማሻሻል መንገዶችን የመለየት ሃላፊነት ያለው ግብረ ሃይል መፍጠርን ያካትታሉ።

## ሰራተኞች እና አስተማሪዎች

የ DCPS ሰራተኞች ልዩ አመለካከቶች የተሰበሰቡት በቨርቿል እና በአካል በተደረጉ ውይይቶች ነበር። **ከሰራተኞች የማዳመጥ ክፍለ ጊዜዎች የተነሱት ጭብጦች—ትምህርት ቤትን መሰረት ያደረጉ እና የማዕከላዊ አገልግሎቶች ግብረ መልስን ጨምሮ—ትክክለኛነትን፣ ፍትሃዊነትን፣ እና ለግብዐቶች ቅድሚያ መስጠትን ይመለከታል።**

የሰራተኞች አባላት ለትክክለኛ አድናቆት እና ስምምነት ለሰራተኞች እና ተማሪዎች ጤናማ እና ጠንካራ አካባቢ በጣም ምቹ እንደሆነ አጋርተዋል። ከወረርሽኙ ጋር በተያያዙ የትምህርት ቤቶች መዘጋት የተፈጠሩትን አለመረጋጋት መጋፈጥ በኋላ፣ ወደ መደበኛ መርሃ ግብር መመለስ ለሰራተኞች አዎንታዊ ነው። በተጨማሪም፣ በየትኛውም የማዕከላዊ አገልግሎቶች እና አቅምን ተገቢ በሆነ መልኩ ለመወሰን የ DCPS የአመራር ቅድሚያ የሚሰጣቸው ፈረቃዎች ዙሪያ በትምህርት ቤት ላይ የተመሰረቱ ሰራተኞችን ለማሳተፍ እና በቅድሚያ ለማሳወቅ ትኩረት ተሰጥቶ ነበር።

ሰራተኞቹ ሁሉም ተማሪዎች በተቻለ መጠን የተሻለውን ትምህርት እንዲያገኙ ያላቸውን ግምት ገልጸዋል። ሰራተኞቹ DCPS በትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ፍትሃዊነትን የሚያሻሽሉ ስልቶችን በመለየት የግብዐት ድልደላዎቹን እንዲመረምር ያላቸውን ፍላጎት አጋርተዋል። ከሰራተኞች የሚቀርቡ ሃሳቦች ሁሉንም ተማሪዎች በብቃት መድረሳቸውን ለማረጋገጥ በፖሊሲዎች እና ልምዶች ላይ በየአመቱ ሃሳብ መግለጽን ያካትታሉ። ለምሳሌ፣ ሰራተኞች በሁሉም የ DCPS ትምህርት ቤቶች ብዙ የገንዘብ ድጋፎች እንዲገኝ የማድረግ አላማ፣ ትምህርት ቤቶች ለተጨማሪ ገንዘብ ለማሰባሰብ የተሻሉ ልምዶችን ከሌሎች ትምህርት ቤቶች ጋር እንዲያጋሩ አጋርተዋል። ሰራተኞች ከDCPS ጋር በፍትሃዊነት ዙሪያ ልምዶቻቸውን እና አመለካከታቸውን ለማካፈል ተጨማሪ እድሎችን ይቀበላሉ።

## ተማሪዎች

ከቨርቿል ክፍለ ጊዜ በተጨማሪ፣ የተማሪ የትኩረት ቡድኖች በሶስት ቦታዎች ተሰብስበው ነበር፦ ከዋልስ ሁከተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ካርዶዞ የትምህርት ካምፓስ፣ እና አናኮስቲያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ከክራመር መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጋር) ውጪ ያለ ትምህርት ቤት

**ተማሪዎች በማህበረሰባቸው የመከባበር እና የመፈለግ አስፈላጊነትን፣ በ DCPS ውስጥ ለበለጠ ፍትሃዊ ፕሮግራም እና ፖሊሲዎችን እንደሚፈልጉ አጋርተዋል፣ እና DCPS እንዲረዳቸው እና ለስኬታቸው እንቅፋቶችን እንዲቀንስላቸው ያላቸውን ፍላጎት አጉልተዋል።**

ተማሪዎች ከመምህራኖቻቸው ጋር እምነት የሚጣልባቸው ግንኙነቶችን ለመገንባት ፍላጎት እንዳላቸው እና እንደ ወጣት ሰዎች ለማደግ በሚያደርጉት ጥረት እየተደገፉ እንደሆነ እንደሚሰማቸው ገለጸዋል። ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጪ ብዙ ፈተናዎች እንደሚገጥሟቸው እና ለታታሪነታቸው እና እድገታቸው አድናቆት እንደሚቸራቸው ተናግረዋል። ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት እንዲረዳቸው በትምህርት ቤት ውስጥ የአዕምሮ ጤና ባለሙያዎችን በደንብ ማግኘት በተማሪዎች ተቀባይነት ያለው እና ደጋፊ አካባቢን ለማጎልበት ሊረዳ ይችላል።

በ DCPS ውስጥ ፍትሃዊ ፖሊሲዎች (እና ተግባራዊነታቸውን) ማረጋገጥ በተማሪ ግብረመልስ ውስጥ ወጥ የሆነ ጭብጥ ነበር። ብዙ ተማሪዎች እንደ የደንብ ልብስ መስፈርቶች እና የጸጉር አሰራር ወይም ሽቶ/ዲኦድራንት ገደቦች ያሉ፣ የአለባበስ ደንብ ስጋቶችን እና እንደዚህ ያሉ መስፈርቶች በተማሪን ባህል ወይም ዳራ የመጣስ አቅም እንዳላቸው ጠቅሰዋል። በስርዐቱ ውስጥ ያሉ ደረጃቸውን የጠበቁ ልምዶች እነዚህን ጉዳዮች ለመቀነስ ይረዳሉ። በተጨማሪ ተማሪዎች አስተያየቶቻቸውን እና አመለካከቶቻቸውን ከርዕሰ መምህራን እና ከ DCPS አመራር ጋር ይበልጥ በመደበኛነት እና ደህንነቱ በተጠበቀ እና ተደራሽ በሆነ መንገድ የሚያጋሩበት መድረክ ላይ ፍላጎት አሳይተዋል።

ተማሪዎች DCPSን ትምህርት ከመጀመሩ በፊት መረጃን ወይም የትምህርት ቀናት የመሳሰሉ፣ ከመካከለኛ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመሸጋገር የሚረዱ መንገዶችን እንዲፈልግ ጠይቀዋል። እንዲሁም ተማሪዎች የትምህርት ቤት ፕሮጀክታቸውን በተሳካ ሁኔታ ለማጠናቀቅ አስፈላጊ የሆኑትን አቅርቦቶች እና መርጃዎች ለማግኘት እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው ገልጸዋል። ችግሮች በሚፈጠሩበት ጊዜ፣ ተማሪዎች ከቅጣት ተኮር መዘዞች ይልቅ ችግሮችን የሚፈቱ የተሃድሶ ፍትሃዊ አማራጮችን ይፈልጋሉ።

ወደ ምረቃ ሲቃረቡ፣ ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኋላ ያላቸውን አማራጮች ሲያስቡ እና ሲያስሱ ተጨማሪ ድጋፍ እና ማበረታቻ ይቀበላሉ። ኮሌጅ ወይም ዩንቨርስቲ ለመማር ለሚያቅዱ ተማሪዎች፣ የካምፓስ ጉብኝቶች ወይም የድጋፍ ግብዐቶችን ጨምሮ፣ ለኮሌጅ እና ለስራ እድሎች ተጨማሪ ዝግጅት፣ ጠቃሚ ይሆናል። አንዳንድ ተማሪዎች የትምህርት ቤታቸውን ኮሌጅ እና የስራ እቅድ አገልግሎቶችን መደገፋቸውን ገልጸዋል እና አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ከሌሎች በሚቀበሉት የመርጃዎች ብዛት ላይ ያለውን ልዩነት ጠቁመዋል። አንዳንዶች የመርጃ ክፍተቱ ከአናኮስቲያ ወንዝ በስተምስራቅ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ስርዐታዊ መሆኑን አቅርበዋል።

> አቃፊ ማህበረሰብ እኔን እንደ ግለሰብ የሚረዳኝ እንጂ – እንደ ተማሪ ብቻ የሚያየኝ አይደለም። እኔ ሰው ነኝ እና በየቤት ስር ማስረከብ የማልችላቸው ስሜቶች አሉኝ።”
>
> - ተማሪ፣ School Without Walls (ስኩልስ ዊዝአውት ዎልስ) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

## ርዕሰ መምህራን

በተሳትፎ ጥረታችን ውስጥ ወሳኝ እርምጃ ከ DCPS ትምህርት ቤት አመራር ግብረ መልስ መሰብሰብ ነበር። **በእነዚህ ክፍለ ጊዜዎች ውስጥ የቀረቡት ዋና ዋና ጭብጦች አካታችነት፣ የትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ እና የአዕምሮ ጤና አገልግሎቶችን ያካትታሉ።**

የDCPS ትምህርት ቤት መሪዎች በትምህርት ቤታችን ማህበረሰቦች ውስጥ ስላለው ፍትሃዊነት እና አካታችነት ዙሪያ እውነተኛ ግብረመልሶችን አጋርተዋል። ብዙዎቹ የአዕምሮ ጤና ግብአቶችን ተደራሽነትን በማሻሻል፣ በተለይም በትምህርት ቤት የምክር አገልግሎት ቦታዎችን፣ አጠቃላይ የተማሪ ፍላጎቶችን ለማሟላት ወሳኝ እንደሆነ ተስማምተዋል። የትምህርት ቤት አመራር ወረርሺኙ ለቤተሰቦች፣ ለመምህራን፣ ለሰራተኞች፣ እና ለተማሪዎች ያልተረጋጋ

ጊዜ እንደሆነ መቀጠሉን፣ እና ብዙ ተማሪዎች መርጃዎቻቸውን የሚያገኙት በትምህርት ቤት ማህበረሰባቸው በኩል ብቻ እንደሆነ አረጋግጠዋል።

DCPS ከቨርቿል ሙሉ በሙሉ በአካል ወደመገኘት ትምህርት ሲሸጋገር፣ የትምህርት ቤት መሪዎች አስተዋይነትን፣ ደግነትን፣ እና አዎንታዊነትን በመለማመድ አዎንታዊ የትምህርት ቤት አካባቢን ማስቀደም ለተማሪ ስኬት አስፈላጊ መሆኑን በከፍተኛ ሁኔታ አጋርተዋል። በተጨማሪ የትምህርት ቤቱ አመራር ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ግቢ እንደገቡ ፣ ይህም በተማሪዎች፣ በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ፣ እና በትምህርት ቤታችን ሰራተኞች መከከል ያለውን ትስስር ለማሻሻል በሰራተኞች በአዎንታዊ እና በደግነት ሰላምታ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ዘርዝረዋል ።

የውይይቱ ትኩረት ወደ ሰራተኞች ሲቀየር፣ የትምህርት ቤት መሪዎች የትምህርት ቤት ሰራተኞችን አስፈላጊነት ገልጸዋል። በቅርብ አመታት ውስጥ፣ እንደ ብዙ የትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች ጉዳይ፣ ሰራተኞችን ማቆየት ለ DCPS ፈታኝ ነበር። እንዲሁም ሰራተኞችን ማቆየት ለአሁኑ ሰራተኞች ተግዳሮቶችን ፈጥሯል፣ ይህም ተጨማሪ ሃላፊነቶችን አስከትሏል። የተሻሻሉ ሰራተኞችን የማቆየት እና የተቀናጀ የቅጥር ጥረቶችን ማረጋገጥ የተማሪን ፍላጎቶች ለማሟላት እና አቅምን በተገቢው ሁኔታ ለማመጣጠን ተጨማሪ የሰራተኞች ድጋፍ እንዲኖር ያስችላል።

“የተማሪዎችን ማንነት የሚያወጡ ሃብቶች… ማንም ሳይፈርድባቸው ያለፈው ታሪካቸውን መናገር ለሚፈልጉ ተማሪዎች ምቹ ሁኔታን መፍጠር።”

- ቤተሰብ/ማህበረሰብ አባል፣ Ron Brown (ሮን ብራውን) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት








# የDCPS ስልታዊ እቅድ የዳሰሳ ጥናት ውሂብ

DCPS ባለ ድርሻ አካላት አስተያየታቸውን ለዲስትሪክቱ የሚያጋሩበትን ተጨማሪ መንገድ ለማቅረብ በስልታዊ እቅድ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች በተመለከተ የመስመር ላይ ዳሰሳ አሰራጭቷል። ጥናቱ የተሰራጨው ኢሜይል እና ድር ጣቢያን ጨምሮ፣ በማህበራዊ ሚዲያ ቻናሎች እና በDCPS ዲጂታል መድረኮች ነው። ከዚህ በታች በአብዛኛው በወላጆች ከተሞላው፣ የዳሰሳ ጥናት የተሰበሰበው መረጃ ማጠቃለያ ነው።

### DCPS ለሁሉም ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ እና ሰራተኞች እንግዳ ተቀባይ እና ደጋፊ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ነው።




### DCPS ሁሉም ተማሪዎች እንዲበለጽጉ ሰራተኞች፣ ቤተሰቦች እና ተማሪዎች የሚፈልጉትን መርጃዎች ያቀርባል።




### DCPS በሁሉም DCPS ፍትሃዊ ፕሮግራምን እና ፖሊሲዎችን ያረጋግጣል።




### የስነ ህዝብ ምርጫዎች




### DCPS ሙሉ አቅማቸው እንዲደርሱ የተማሪዎችን ፍላጎቶች በትምህርት፣ በማህበራዊ፣ እና በስሜት ይደግፋል።




### የዳሰሳ ጥናት ተሳታፊዎች



**አብዛኞቹ የዳሰሳ ጥናት ምላሽ ሰጪዎች ከሚከተሉት ትምህርት ቤቶች ጋር ትስስር ነበራቸው፦**

- ጃክሰን ሪድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ዲል መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ማውሪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ዋይቲየር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- Columbia Heights Education Campus (ኮሎምቢያ ሂይትስ የትምህርት ካምፓስ)
- Duke Ellington School of the Arts (ዱክ ኤሊንግተን ስኩል ኦፍ አርትስ)
- ባንከር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ሃርዲ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ላፋይቲ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

"ሁሉም ተማሪዎች ስኬታማ መሆናቸውን ለማረጋገጥ አስተማሪዎችን፣ ቴራፒስቶችን እና በድጋሚ ተማሪዎችን ድምጽ የሚያዳምጡ ሰዎችን/አዋቂዎችን እና እንደ ተማሪ የምንናገረው ነገር እንዲሰማ እና ዋጋ እንዲሰጠው እንፈልጋለን።"

- ተማሪ፣ Anacostia (አናኮስቲያ) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት / ክራመር መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ክፍለ ጊዜ

# ቀጣዩ ምንድን ነው?

የግብረ መልስ ምልልሱን መዝጋት የስልታዊ እቅድ ሂደታችን አስፈላጊ እርምጃ ሲሆን፣ የተሳትፎ ግቦቻችንን ለመፈጸም ወሳኝ ነው። ከባለ ድርሻ አካላት ጋር የነበረን ተሳትፎ በርካታ የተጨባጭ፣ እና የተግባራዊ ግብረ መልስ ምሳሌዎችን ሰጥቶናል። በተሳትፎው ምዕራፍ ወቅት ከባለ ድርሻ አካላት የሰማነው እና በዚህ ሪፖርት ያጋራንዎት አብዛኛው ነገር የስልታዊ እቅዱን አቅጣጫ ለማሳወቅ ይጠቅማል። የተሳትፎ ምዕራፉን ስናጠናቅቅ እና ወደ ቀረጻ እና ንድፍ ስንሸጋገር፣ ቀጣዩ ምዕራፍ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለንን ግንኙነት በሚያጠናክሩ የተሳትፎ እድሎች ለመቀጠል መዘጋጀቱን ለDCPS ማህበረሰብ ማረጋገጥ እንችላለን።







# ስለ ቁርጠኛነትዎ እና ተሳት ፎዎ እናመሰግናለን!



## ከእኛ ጋር ይገናኙ

1200 First Street, NE, Washington, DC 20002

ስልክ፦ (202) 442-5885

ድረገጽ፦ dcps.dc.gov

@DCPublicSchools

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR